በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 214325

ግንቦት 2 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ለምለም ቅጣው- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘቢባ የሱፍ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በቀን 14/01/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0332243 በቀን 21/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በስር የደዋ ጨፋ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪ በቀን 09/06/2012 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አባቴ የሱፍ ኢብራሂም በቀን 05/05/1987 ዓ.ም በሞት ተለይቷል። የአባቴን ወራሽነት በደዋ ጨፋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0302372 አረጋግጫለሁ። አባቴ በህይወት ሲኖር ተከሳሽን አግብቶ 6 ልጅ

ያላቸው ሲሆን እኔ ደግሞ ከበፊት ሚስቱ ወ/ሮ ሀሊማ ኡስማን የወለደኝ ስሆን አባቴ በህይወት እያለ በከሚሴ ከተማ ውስጥ 528 ካ.ሜ በሆነ ቦታ ላይ የሚገኝ 1 ትልቅ ቆርቆሮ ቤት በውስጡ 2 ክፍል ያለው፣ 1 ትልቅ ቆርቆሮ ቤት 6 ክፍል ያለው እንዲሁም 6 ክፍል ሰርቪስ ቤት ያለው ሁሉንም በጋራ አፍርተዋል። አባቴ ሲሞት ህጻን ስለነበርኩ ካደኩኝ በኋላ በተከሳሽ ስር እንደ ወላጅ እናት በማየት በፍርሀትና በማክበር ክስ ሳላቀርብ ቆይቼ ንብረት እንድታካፍለኝ በሽማግሌ ብጠይቅም ለማካፈል እንቢ ስላለች የውርስ ንብረት ድርሻዬን እንድታካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ተከሳሽ በሰጡት መልስ የቀረበው ክስ በ15 አመት ይርጋ ይታገዳል፤ የከሳሽ አባት የሞተው በ1987 ዓ.ም ሲሆን የከሳሽ እድሜ በግዜው 15 አመት ነበር፤ 18 አመት የሚሞላት በ1991 ዓ.ም ነው። ከዚህ አመት ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም መጠየቅ ነበረባት። ስለሆነም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል። በሌላም በኩል ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሳሽን እንደ ልጄ ሳሳድጋት እንደነበርና በራሴ ወጪ የዳርኳት መሆኑን እሷም አትክድም፤ የምታገኘው የውርስ ድርሻ በግዜው የቤቱን ዋጋ በሽማግሌ ተገምቶ እና ከእኔ የሚወለዱ 7 ልጆች ስላሉ የእሷ ድርሻ ብር 3000.00 (ሶስት ሺህ) ከተወሰነላት በኋላ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ከእኛ ጋር ኖራለች በዚህ አመት ውስጥ የድርሻ ገንዘቡን ጨምረን 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ) ስንሰጥ ከሳሽ እንዴት ከወንድሞቼ እለያለሁ ወንድሞቼ ይበልጡብኛል በማለት አልወሰደችም። ስለሆነም ፍርድ ቤቱ እኔው ጋር መኖሯን ተረድቶልኝ እንዲሁም ስራ እሰራለሁ በማለት ገንዘብ መውሰዷ ታይቶ ከክሱ በነፃ እንድሰናበት በማለት ተከራክረዋል።

የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የከሳሽ አባት የሞተ በ1987 ዓ.ም መሆኑና ክርክር ያስነሳው ንብረት በተከሳሽ እጅ መኖሩ ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም። ከሳሽ በ1995 ዓ.ም እድዋ 18 ዓመት ስለሚሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ መቅረብ ያለበት በ15 አመት ውስጥ ነበር፤ ይሁን እንጂ ክስ ያቀረበችው እድሜዋ ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች በኋላ 18 አመት ቆይታ በካቲት 9 ቀን 2012 ዓ.ም ነው። ስለሆነም የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ይግባኝ ለኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ክርክራቸውን ሰምቶ የከሳሽ የውርስ መብት በይርጋ የታገደ ነው በማለት ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

በመጨረሻ ከሳሽ ቅሬታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ አጣሪ ችሎቱ ቅሬታውን መርምሮ ተከሳሽ ከሰጡት መልስ አንጻር የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለውን ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ሰበር ችሎቱም የግራቀኙን ክርክር ተመልክቶ ከሳሽ በሚያከራክረው ቤት ላይ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የምትጠቀምበት እንደነበር እንዲሁም በየግዜው ተከሳሽ ገንዘብ ትሰጣት እንደነበር በመልስዋ ላይ መግለጽዋ ሲታይ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ያለውን ጊዜ ይርጋ ማቋረጫ ምክንያት እንደሚሆን ከፍ/ብ/ሕ/ህ/ቁ 1851፣ 1852 መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ በፍሬ ነገሩ ላይ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በቀን 14/01/2014 ዓ/ም ያቀረቡት ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡትን ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የወሰኑትን የክልሉ ሰበር ችሎት በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወደስር ፍርድ ቤት በመመለስ የወሰነበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው አንድን ክስ ለማቅረብ በህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ለማቅረብ የማይቻል ቢሆንም ህጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች የይርጋው ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል እና አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር እንደሚጀምር በፍ/ብ/ህ/ቁ 1852(1) ሥር ተመልክቷል፡፡ በተለይ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በውርስ ንብረት በጋራ ሲገለገሉ መኖር እንዲሁም ከውርስ ንብረት ዕዳን አምኖ ክፍያ ለመፈፀም ፈቅዶ በዚሁ አግባብ ሲከፈል መኖር ይርጋ ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከፍሲል እንደተገለፀው ተጠሪ የሟች ልጅ እና ወራሽ መሆኗ፤ ከልጅነቷ ጀምሮ ከአመልካች ጋር በአከራካሪው ቤት እስከ 2004 ዓ.ም እና ከዚያም በኃላ እየተጠቀመች መኖሯ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ አመልካችም በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህም ሌላ አመልካች የውርስ ሀብት ድርሻዋን እንድትወስድ በአመልካች ስትጠየቅ የነበረ መሆኑ እና በሽማግሌ ድርሻዋ ከተወሰነላት በኋላ አልወስድም ስላለች ለስራ መጀመሪያ በሚል የውርስ ድርሻን ታሳቢ በማድረግ ገንዘብ ይሰጧት እንደነበርም አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በውርስ ንብረቱ መገልገል ያቋረጠችበት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ (ወደ ሳውዲ አረቢያ ሄደች ከተባለችበት) ነው ቢባል እንኳ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር እንደሚጀምር የክልሉ ሰበር ችሎት የደረሰበት መደምደሚያ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ክርክሩ ወራሽ በሆነችው ተጠሪ እና ወራሽ ባልሆኑት አመልካች መካከል በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000 መሰረት የይርጋ ጊዜው 10 (አስር) አመት ነው፡፡ አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ከጀመረበት ክስ እስከቀረበበት በካቲት 9 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ሲሰላ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም፡፡

ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍ/ቤት ፍሬ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን መመለሱ ከፍሲል የተገለፁትን የህጉን ድንጋጌዎች እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0332243 በቀን 21/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት በውጤቱ ፀንቷል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

2. የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የታገደ አይደለም ተብሎ የፍሬ ነገር ክርክሩ ታይቶ እንዲወሰን ጉዳዩ ለስር ፍርድ ቤት በመመለስ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

3. ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም